ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 130 ጥር 10 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## የጥምቀት በዓል ለሌሎች ሀገር በቀል ቅርሶች እድገት ጉልህ ሚና አለው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የጥምቀት በዓል በዓለም ቅርስነት የተመዘገበ በመሆኑ ለሀገር ኢኮኖሚ፣ ለቱሪዝም ዘርፍ እና ለሌሎች የአደባባይ በዓላት እድገት ጉልህ ሚና አለው ሲሉ ከፍተኛ የቱሪዝም ባለሙያው ዶክተር አያሌው ሲሳይ ተናገሩ።

ከፍተኛ የቱሪዝም ባለሙያው ዶክተር አያሌው ሲሳይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የጥምቀት በዓል በዓለም ቅርስነት የተመዘገበ በመሆኑ ለሌሎች አደባባይ በዓላትና ለማይዳሰሱ ቅርሶች እድገት ጉልህ ሚና አለው። የጥምቀት በዓል ኢትዮጵያን በአለም ገበያ እንድትታዋወቅ አድርጓል። ይህም ለሌሎች የሀገር ውስጥ ቅርሶች እድገት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው።

"የአደባባይ በዓላት አለም አቀፍ ቱሪስቶችን የመሳብ አቅም አላቸው፤ የጥምቀት በዓልም ወደ ኢትዮጵያ ቱሪስትን ለመሳብ የምንጠቀምበት አንዱና ዋነኛው የአደባባይ በዓል ነው" ያሉት ዶክተር አያሌው፤ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች የጥምቀት በዓል አከባበርን ከመታደም


የጥምቀት በዓል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል የጥምቀትና የከተራ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ ዝግጅት ማድረጉን ገለጸ

### - ግብረ ኃይሉ በሰላም ዙሪያ ከሃይማኖት አባቶች ጋር ተወያይቷል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል የከተራና የጥምቀት በዓላት በሰላም እንዲከበሩ ዝግጅት ማድረጉን አስታወቀ፡፡ ግብረ ኃይሉ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ


የፀጥታና ደኅንነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ምክር ቤቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንት ሹመትን አጸደቀ

በጌትነት ተስፋማርያም



አዲስ አበባ ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሹመትን አጸቀደ። በዚህም መሰረት ረዳት ፕሮፌሰር ቴዎድሮስ ምህረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፤ ወይዘሮ አበባ እምቢአለ ደግሞ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ተሹመዋል።

የኢፌዲሪ ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለተኛ ዓመት የስራ ዘመን ስምንተኛ መደበኛ ስብሰባውን ትናንት አካሂዷል።

በወቅቱ የቀድሞው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መዓዛ አሸናፊና ምክትል ፕሬዚዳንቱ


ምክር ቤቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## "ኀልቶ የወጣው የፖለቲካ ገበያ አዝማሚያ በጋራ ካልተመከተ የከፋ ጉዳት ያስከትላል"

- አቶ ተስፋዬ በልጅጌ
በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር

ምሕረት ሞገስ

አዲስ አበባ፡- ኀልቶ የወጣውን የፖለቲካ ገበያ አዝማሚያ ኢትዮጵያውያን በጋራ መክተን መልክ ካላስያዝነው የከፋ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ፤ ህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረውና እንዲረዳው፤ በጋራም እንዲመክት እየተሠራ መሆኑን አቶ ተስፋዬ በልጅጌ ተናገሩ፡፡

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ገበያ አዝማሚያ


"ኀልቶ የወጣው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






















የጥምቀት ትውፊቱ ሸማና ጥለቱ
ገጽ 3